# FY18 የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ እቅድ
# DeKalb County የት/ቤት አውራጃ ደረጃ
# የትምህርት አመት 2017-2018

## የክለሳ ቀን፡ ሴፐቴምበር 20/2017

የተማሪዎችን ትምህርት ስኬታማነት ለማጠንከር ታስቦ DeKalb County ት/ቤት አውራጃርዕስ I፣ ክፍል ሀ እርዳታ ያገኛል፤ ስለሆነም ከተሳታፊ ልጆች ወላጆች እና ቤተሰብ አባላት ጋር በመሆን እያንዳንዱ ተማሪ ስኬታማ ይሆናል የሚለው ህግ (ESSA) ክፍል 1116(a) (2) የሚያስገድደውን መረጃ የሚይዝ የጽሁፍ የወላጆች እና ቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲ በጋራ ማዘጋጀት፣ መስማማት እና ማከፋፈል አለብን። ፖሊሲው ትርጉም ያለው የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ እንዲኖር የLEAን ስራ እና አላማ ያዘጋጃል እንዲሁም እንዴት LEA ብዙ የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን እንደሚተገብር ይገልጻል፤ በተጨማሪ ፖሊሲው ለGeorgia የትምህርት መምሪያ የገባው የLEA እቅድ ላይ የተካተተ ነው።

**DeKalb County ት/ቤት አውራጃ በክፍል 1116 ላይ በተገለጸው መሰረት የሚከተሉትን መስፈርቶች ለመተግበር ተስማምቷል፡**

- የት/ቤቱ አውራጃ በርዕስ I፣ ክፍል ሀ ት/ቤቶቹ ሁሉ የሚገኙትን ወላጆች እና የቤተሰብ አባላት ለማሳተፍ መርሀግብሮችን፣ እንቅስቃሴዎችን እና አሰራሮችን ስራ ላይ ያውላል። እነዚህ መርሀግብሮች፣ እንቅስቃሴዎች እና አሰራሮች የሚታቀዱት እና ስራ ላይ የሚውሉት ከተሳታፊ ልጆች ወላጆች እና የቤተሰብ አባላት ጋር በመማከር ነው።

- ክፍል 1116ን በማክበር የት/ቤት አውራጃው አስፈላጊው የት/ቤት-ደረጃ የወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲዎች የ ESSA ክፍል 1116 (b) መስፈርቶች ማሟላታቸውን ለማረጋገጥ ከት/ቤቶቹ ጋር በጋራ ይሰራል እንዲሁም እያንዳዱ ት/ቤት በ ESSA ክፍል 1116 (d) መሰረት የት/ቤት/ወላጅ ትስስር ይይዛል።

- የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ርዕስ I፣ ክፍል ሀ መስፈርቶች በተቻለ መጠን በሚተገበርበት ወቅት የት/ቤቱ አውራጃ እና ት/ቤቶቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ለሌላቸው፣ መጻፍ እና ማንበብ ለማይችሉ፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለስደተኞች ልጆች፣ ለችግረኞች ልጆች ወይም ማንኛውም አናሳ የዘር ወይም ጎሳ ትውልድ ላላቸው እንዲሳተፉ ሙሉ እድል ይሰጣሉ፤ እንዲሁም በESSA ክፍል 1111 የሚጠየቀውን መረጃ እና የት/ቤት ሪፖርትን በሚገባ እና ተመሳሳይ አቀራረብ እንዲሁም በአማራጭ አቀራረብ በተቻለ መጠን ወላጆች በሚገባቸው ቋንቋ መስጠት ጨምሮ።

- በ ESSA ክፍል 1112 ስር የተዘጋጀው የርዕስ I፣ ክፍል ሀ የ LEA እቅድ ለተሳታፊ ልጆች ወላጆች አጥጋቢ ካልሆነ የት/ቤት አውራጃው እቅዱን ለክልሉ የትምህርት መምሪያ በሚያስገባበት ወቅት ማንኛውንም የወላጅ አስተያየት ከእቅዱ ጋር ያስገባል።

- የት/ቤቱ አውራጃ በሚከተሉት የወላጅ ተሳትፎ ትርጉም ይተዳደራል እንዲሁም የርዕስ I ት/ቤቶቹን መርሀግብሮችን፣ እንቅስቃሴዎችን እና አሰራሮችን በESSA ክፍል 8101 ላይ በተተረጎመው መሰረት እንዲፈጽሙ ይጠብቃል፡፡

የወላጅ ተሳትፎ ማለት ወላጅ በመደበኛ፣ የሁለትዮሽ እና ትርጉም ያለው እንዲሁም የተማሪውን የመማር እና ሌላ የት/ቤት እንቅስቃሴዎች ያካተተ ንግግር፣ ማረጋገጥን ጨምሮ መሳተፍ ማለት ነው፡፡

ሀ. ወላጆች የልጆቻቸውን የመማር ሂደት በማገዝ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ
.ለ. ወላጆች በልጆቻቸው የት/ቤት ትምህርት ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ
ሐ. ወላጆች በልጆቻው ትምህርት ሙሉ ሸሪክ ሲሆኑ በልጆቻቸው ትምህርት ላይ እንዲያግዙ በተቻለ መጠን በውሳኔዎች እና በአማካሪ ኮሚቴ ውስጥ ይካተታሉ
መ. ሌሎች እንቅስቀሴዎች ለምሳሌ በ ESEA ክፍል 1116 ላይ የተገለጹት አይነት ይደረጋሉ

## አውራጃው አስፈላጊውን የ LEA የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ ስራዎችን እንዴት እንደሚተገብር ገለጸ

### የ DEKALB COUNTY ት/ቤት አውራጃ

**ራእይ**
የሚማር ማህበረሰባችንን በትምህርት የበለጠ ብቃት እንዲኖረው ማነቃቃት

**ተልዕኮ**
ወደከፍተኛ ትምህርት፣ ስራ እና የእድሜ-ልክ ትምህርት በማምራት የተማሪ ስኬትን ማረጋገጥ፡፡

**መርህ**
ማነቃቃት፣ ማስቻል እና መብለጥ

---

**የግብ ቦታ 1፡ ከፍትህ እና ተደራሽነት ጋር የተማሪ ስኬት**
**የተማሪ የመማር ችሎታ ደረጃን ማሻሻል**

የDeKalb County የት/ቤት አውራጃ በGeorgia Milestones የስነ-ጥበብ የክፍል የመጨረሻ (EOG) ግምገማ የተማሪዎችን ውጤት ፐርሰንት በታዳጊ ተማሪ ደረጃ ወይም ከዛ በላይ ይጨምራል፡፡

የ DeKalb County የት/ቤት አውራጃ በ Georgia Milestones የሂሳብ የክፍል የመጨረሻ (EOG) ግምገማ የተማሪዎችን ውጤት ፐርሰንት በታዳጊ ተማሪ ደረጃ ወይም ከዛ በላይ ይጨምራል፡፡

***በጋራ የተዘጋጀ***

**<u>DeKalb County ት/ቤት አውራጃ</u>**በጋራ በተዘጋጀው በክፍል 1112 የLEA የወላጆች ተሳትፎ እቅድ እና የESEA ክፍል 1116 የት/ቤት ግምገማ እና ማሻሻያ ሂደት ላይ ወላጆች እንዲሳተፉ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፡

ወላጆች የአውራጃው የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ፣ CLIP እና ርዕስ I የመላው ት/ቤት/ት/ቤት-ተኮር እገዛ እቅድ ሲዘጋጅ እና ሲገመገም በሚከተለው መንገድ እንዲሳተፉ እድል ይሰጣቸዋል፡

- የርዕስ 1 ሚመለከታቸው አካላት (በቀድሞው ስሙ ቅድመ-እቅድ) ስብሰባ፡፡
- አጠቃላይ ፍላጎቶች ግምገማ (CNA) ስብሰባ
- ከወላጆች ጋር በድህረ-ገጽ እና በተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን አይነቶች መነጋገር፡፡

***የቴክኒክ እገዛ***

**<u>DeKalb County የት/ቤት አውራጃ</u>**የተማሪ የትምህርት ስኬት እና ብቃት ለማሻሻል ማለትም ከቀጣሪዎች፣ ከንግድ መሪዎች እና ፊላንትሮፒክ ድርጅቶች ወይም ወላጆች እና የቤተሰብ አባላት ትምህርት ላይ በስኬታማነት እንዲሳተፉ የሚያስችሉ ባለሙያ ሰዎች ጋር ትርጉም ያለው መመካከርን ባካተተ መልኩ የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ እና በስኬታማነት ለመተግበር የሚከተሉትን ትብብር፣ የቴክኒክ እገዛ እና የሁሉንም ርዕስ I፣ ክፍል ሀ ት/ቤቶች ለማገዝ እና አቅም ለመገንባት የሚያስፈልጉ ሌሎች እገዛ ይሰጣል፡
:

የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎችን ለማቀድ እና በስኬታማነት ለመተግበር፤ የት/ቤት የወላጅ ተሳትፎ እቅድ፣ ት/ቤት-ወላጅ ትስስር እና ሁሉንም የርዕስ I የወላጅ ተሳትፎ መስፈርቶችን ጨምሮ ለሁሉንም ርዕስ I ት/ቤቶቹ እገዛ እና የቴክኒክ እርዳታ በሚከተለው ይሰጣል፡፡

-የማዕከላዊ ጽ/ቤት እገዛ ለወላጅ ተሳትፎ - (የርዕስ I ዳይሬክተር፣ ረዳት ዳይሬክተር፣ የOFP አስተባባሪ፣ የአውራጃ የወላጅ ተወካይ እና አስተዳደራዊ እገዛ)
- የወላጅ ተሳትፎን የሚደግፉ አምስት በአውራጃ-ደረጃ የሚገኙ ማዕከላት፡፡
- በት/ቤቶች-በት/ቤት ደረጃ ባሉ የወላጅ ጽ/ቤቶች የታገዘ የአካባቢ የወላጅ ማዕከል፡፡
- የርዕስ l የቴክኒክ እገዛ እና ስራ
- ርዕስ l የማክበር እና መመሪያ ስብሰባ (Ed Camp)
- የርዕስ l ማሻሻያዎችን ለማጋራት በርዕሰ መምህር ስብሰባ የርዕስ l ተሳትፎ

***አመታዊ ግምገማ***

**<u>DeKalb County ት/ቤት አውራጃ</u>**የርዕስ I፣ ክፍል ሀ ት/ቤቶቹን የትምህርት ጥራት ለማሻሻል የወላጆች እና የቤተሰብ አባላት ትርጉም ያለው ተሳትፎ ተጨምሮበት የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲው ይዘት እና ውጤታማነት አመታዊ ግምገማ ለማድረግ የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፡ ግምገማው ወላጆች እንቅስቃሴው ላይ በደንብ እንዳይሳተፉ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮችን ለማወቅ ነው (በተለይ ችግረኛ፣ አካል ጉዳተኛ፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችግር ያለባቸው፣ መጻፍ እና ማንበብ የማይችሉ ወይም አናሳ የዘር ወይም ጎሳ ትውልድ ያለባቸው ወላጆች ላይ ትኩረት ይደረጋል)፡፡ በተጨማሪ ግምገማው የወላጆች እና የቤተሰብ አባላት ልጆቻቸውን በትምህርት ለማገዝ የሚያስፈልጋቸውን ማለትም ስኬታማ የት/ቤት እና የቤተሰብ ግንኙነቶችን ለመደገፍ ከት/ቤት ሰራተኞች እና መምህራን ጋር አብሮ መስራትን እንዲሁም ስልቶችን በመጠቀም መስራትን ጨምሮለማወቅ ይረዳል፡፡ የት/ቤት አውራጃው ስለወላጅ እና የቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲው ባደረገው ግምገማ ያገኘውን ግኝት የበለጠ ውጤታማ

የወላጅ ተሳትፎ ለማምጣት እና አስፈላጊ ከሆነ የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ፖሊሲውን ለመከለስ የሚያስችል ማስረጃ-ተኮር የሆነ ስልት ለመቅረጽ ይጠቀምበታል፡፡

| |
|---|
| በDCSD የሚደረገው የርዕስ I መርሀግብር ግምገማ የሚከተሉትን ያካተተ ነገር ግን በዚህ ብቻ ባልተገደበ ብዙ ስልቶችን በመጠቀም ይደረጋል፡<br><br>- በስርአተ-ትምህርት፣ ትምህርት እና የሙያ ትምህርትዋና ዳይሬክተር እና የፌደራል መርሀግብሮች ጽ/ቤት በተዘጋጀው መሰረት የገንዘብ እና መርሀግብር የማጠናቀቅ ግምገማ፡፡<br><br>- በአውራጃ-ደረጃ ከተደረገ የጥናት ዳሰሳ የወላጆች አስተያየት፡፡<br><br>- በቅድመ-እቅድ የአውራጃ እና የት/ቤት ደረጃ ስብሰባዎች ላይ የተገኘ የወላጅ ግብአት በአውራጃ-ደረጃ ከተደረገ የጥናት ዳሰሳ የወላጆች አስተያየት፡፡ |

**የገንዘብ አያያዝ**

**<u>DeKalb County ት/ቤት አውራጃ</u>**በርዕስ I፣ ክፍል ሀ ት/ቤቶች የሚማሩ ልጆች ወላጆች እና የቤተሰብ አባላትን ለወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ተብሎ ከርዕስ I፣ ክፍል ሀ 1 በመቶ የተያዘው ገንዘብ እንዴት ወጪ እንደሚሆን የሚደረጉ ውሳኔዎች ላይ ያሳትፋል እንዲሁም ከ1 በመቶው ላይ ከተያዘው ገንዘብ ከ90 በመቶው ያላነሰው ገንዘብ በቀጥታ ለርዕስ I ት/ቤቶች ወጪ መደረጉን ያረጋግጣል፡፡

| |
|---|
| DCSD ለርዕስ I የተያዘ የገንዘብ በጀትን በሚከተሉት የተለያዩ መንገዶች ይጠቀማል፡<br>**ደሞዝ**<br>የአውራጃ ወላጅ አመቻች<br><br>**አውርቦት/ምንጭ**<br>በአውራጃ-ደረጃ የወላጅ ማእከላት<br>በአውራጃ-ደረጃ የወላጅ ወርክሾፕ<br>ርዕስ l የማክበር እና መመሪያ ስብሰባ<br><br>**ግንኙነት**የርዕስ I ግንኙነቶች እና ሰነዶች በዋና 10 ቋንቋዎች<br>ለአውራጃ ወላጅ ስብሰባ አስተርጓሚ (CLIP፣ የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ)<br><br>**ሌላ**<br>በአውራጃ-ደረጃ የሚደረግ የርዕስ I ወላጅ ስብሰባ<br>የወላጅ አመቻች ጉዞ ወጪ ተመላሽ<br><br>DCSD በሚከተለው ወቅት ወላጆች ስለርዕስ I የገንዘብ አያያዝ አጠቃቀም በተመለከተ እንዲሳተፉ እና ግብአት (ምክር/አስተያየት) እንዲሰጡ እድል ይሰጣቸዋል፡<br>- የርዕስ I ቅድመ-እቅድ የአውራጃ ስብሰባ<br>- የርዕስ I የት/ቤት ደረጃ የማህበረሰብ ስብሰባ<br>- የአውራጃ የወላጅ ወርክሾፕ/ስልጠና |

**የአገልግሎቶች ትብብር**

የ **DeKalb County ት/ቤት አውራጃ** በተቻለ እና አግባብ በሆነ መጠን የወላጅ እና ቤተሰብ ተሳትፎ ስልቶችን ከሚከተሉት ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት የበለጠ እንዲሳተፉ ከሚያበረታቱ እና ከሚደግፉ ሌሎች ከሚመለከታቸው የፌደራል፣ ክልል እና የአካባቢ ህጎችእና መርሀግብሮች ጋር በማስተባበር ያጣምሻል፡፡

1. ከፌደራል መርሀግብሮች ጽ/ቤት (OFP) እገዛ ይሰጣል።
2. በአምስቱ ክልላዊ ማዕከላት እና ሰላሳ ስድስት የት/ቤት ማዕከላት ለሚገኙት ማዕከላት ወላጆች ተደራሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል።
3. የክልል ማእከላት የማህበረሰቡን፣ ወላጆች እና የሚመለከታቸው አካላት ፍላጎት ለማሟላት በሳምንት አንድ ቀን ማብቂ ሰአትን ማራዘም፡፡

**ወላጆችን አቅም መገንባት**

**DeKalb County ት/ቤት አውራጃ**በርዕስ I ት/ቤቶቹ በመታገዝወላጆች ከልጆቻቸው ጋር መስራት እዲችሉ እና የልጆቻቸውን የትምህርት ስኬታማነት ማሻሻል እንዲችሉ የመጻፍ እና ማንበብ ስልጠና እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ (የባለቤትነት ሙብት ጥሰት ጉዳት ትምህርትን ጨምሮ) የሚነበቡ ጽፎችን እና ስልጠናዎችን በመስጠት የበለጠ የወላጅ ተሳትፎ ለማግኘት የወላጆችን አቅም ይገነባል፡፡ እንዲሁም ወላጆች የሚከተሉትን ርዕሶች እንዲረዱ እገዛ ይሰጣል፡

- ከባዱን የክልል የትምህርት ደረጃ
- የክልል እና አካባቢ ትምህርት ግምገማ፤ አማራጭ ግምገማን ጨምሮ
- የርዕስ 1፣ ክፍል ሀ መስፈርቶች
- የልጃቸውን ለውጥ እንዴት መቆጣጠር እንደሚችሉ
- ከአስተማሪዎች ጋር እንዴት በጋራ መስራት እንደሚችሉ

ወላጆች የልጆቻቸውን የትምህርተ ስኬት በመርዳት ረገድ ለማገዝ ወርክሾፕ/ዝግጅት፣ ትምህርት፣ ምንጭ እንዲሁም የሚከተሉትን ጨምሮ ይሰጣል፡

1. ርዕስ l የወላጅ ተሳትፎ ስብሰባ (የአውራጃ እና የክልል)።
2. አጠቃላይ የ LEA ማሻሻያ እቅድ (CLIP)(አመታዊ)።
3. ርዕስ l የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ ስብሰባ (አመታዊ)።
4. የወላጅ ወርክሾፖች (ለምሳሌ Georgia Milestone፣ Infinite Campus ወዘተ)
5. በአውራጃ-ደረጃ የሚደረግ ርዕስ I የወላጅ ስብሰባ።

**የት/ቤት ሰራተኞችን አቅም ግንባታ**

**DeKalb County ት/ቤት አውራጃ**በት/ቤቶቹ እና ወላጆች በመታገዝ መምህራኖቹን፣ ልዩ የትምህርት ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞቹን፣ ርዕሰ መምህራኑን እና ሌላ የት/ቤት መሪዎችን እንዲሁም ሌላ ሰራተኞችን ስለወላጅ ተሳትፎ ዋጋ እና ጥቅም፤ እንዴት ወላጆችን ማግኘት፣ ማነጋገር እና ሸሪክ ሆኖ አብሮ መስራት እንደሚቻል፣ የወላጅ መርሀግብሮችን እንዴት እንደሚተገብሩ እና እንደሚያስተባብሩ እንዲሁም በወላጆች እና ት/ቤቶች መካከል ትስስር እንደሚፈጥሩ በሚከተሉት ያስተምራል፡

አውራጃዎች እና/ወይም ት/ቤቶች በሚከተሉት በስብሰባ፣ ወርክሾፖች፣ ስልጠና፣ ዌባይነር እና ወላጆች ሸሪክ ሆነው ለመስራት በሚያስችላቸው ምንጮች አቅማቸውን ይገነባሉ፡

1. የት/ቤት አስተዳደሮች/ርዕሰ ምምህራን እና/ወይም የተወከሉ ሰራተኞች ወርሀዊ ስብሰባ
2. በርዕስ I ለሚደጎም ሰራተኛ የባለሙያ ሰራተኛ።
3. ርዕስ 1 የማክበር እና መመሪያ መርሆዎች ከፍተኛ ስብሰባ

አውራጃው እና ት/ቤቶች የት/ቤት እና ወላጆች መርሀግብሮችን፣ ስብሰባዎችን እና ሌላ እንቅስቃሴዎችን በተመለከተ ለወላጆች በተቻለ መጠን በሚገባቸው አይነት እና ቋንቋ መረጃ ይሰጣሉ፡፡

**ተሳትፎን ለመጨመር አቅም ግንባታ**

- ☐ የመምህራን፣ ርዕሰ መምህራን እና ሌላ አስተማሪዎች ስልጠና ሲዘጋጅ የስልጠናውን ውጤታማነት ለመጨመር ወላጆችን ማሳተፍ
- ☐ የት/ቤት አውራጃው የመጻፍ እና ማንበብ ስልጠና ለወላጆች ለመስጠት ያሉትን ምክንያታዊ የገንዘብ ምንጮች በሙሉ ፈልጎ ካጣ በኋላ በርዕስI፣ ክፍል ሀ ገንዘብ አስፈላጊውን ስልጠና መስጠት
- ☐ ወላጆች ከት/ቤት ጋር የተያያዙ ስብሰባዎች እና ስልጠናዎችን መካፈል እንዲችሉ ከወላጅ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ ማለትም መጓጓዣ እና የልጅ እንክብካቤ ወጪዎችን ጨምሮ ምክንያታዊ እና አስፈላጊ ወጪዎችን መክፈል
- ☐ የሌላ ወላጆች ተሳትፎ እንዲጨምር ወላጆችን ማሰልጠን
- ☐ ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርትያላቸውን ተሳትፎ መጨመር፣ የት/ቤት ስብሰባዎችን በተለያየ ጊዜ ማዘጋጀት ወይም በመምህራን ወይም ከተሳታፊ ልጆቹ ጋር በቀጥታ ከሚሰሩ ሌሎች አስተማሪዎች እና ት/ቤት የሚደረጉትን ስብሰባዎች መካፈል በማይችሉ ወላጆች መካከል የቤት ውስጥ ስብሰባ ማድረግ
- ☐ የወላጅ ተሳትፎን ለማሻሻል የሙከራ ስልቶችን ማዘጋጀት እና መተግበር
- ☐ በአውራጃ-ደረጃ የሚያገለግል እና በርዕስ I፣ ክፍል ሀ መርሀግብሮች የወላጅ ተሳፎ ላይ ስለሁሉም ጉዳዮች የሚያማክር አማካሪ ኮሚቴ ማዘጋጀት
- ☐ በወላጅ ተሳትፎ እንቅስቃሴ ላይ ማህበረሰብ-ተኮር የሆኑ ድርጅቶች እና ንግዶች፤ እምነት-ተኮር ድርጅቶችን ጨምሮ ተገቢ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ

**<u>በስራ ላይ መዋል</u>**

ይህ የ LEA የወላጅ ተሳትፎ ፖሊሲ በጋራ ተዘጋጅቶ በርዕስ I የሚመለከታቸው አካላት ስብሰባ፣ በአጠቃላይ የፍላጎት ግምገማ ስብሰባ ወቅት እና ከወላጆች ጋር በት/ቤት/አውራጃ ድህረ-ገጽ እና የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀን መንገዶች በተደረጉት ግንኙነቶች ወቅት የሚመለከታቸው አካላት አስተያየት ታክሎበት በርዕስ I፣ ክፍል ሀ መርሀግብር በሚሳተፉ ልጆች ወላጆች ጋር ስምምነት ተደርጓል፡፡

ፖሊሲው/እቅዱ ለመጀመሪያ ጊዜ ወላጆች እና የሚመለከታቸው አካላት አስተያየት እንዲሰጡበት የቀረበው በጁላይ 13/2017 ነው፡፡ በጁላይ 31/2017 ከወላጅ በተገኘ መረጃ ክለሳ ተደርጎበት በኦገስት 7/2017 ቀርቧል በመቀጠልም በ<u>09/20/17</u> በ GaDOE CLIP አስተያየቶች ተሻሽሎ በ DeKalb County ት/ቤት አውራጃ ጸድቋል፡፡ ይህ ፖሊሲ/እቅድ ከኦገስት 2017-ኦገስት 2018 ድረስ በስራ ላይ ይቆያል፡፡ ት/ቤት አውራጃው ፖሊሲውን ለሁሉብ በርዕስ I፣ ክፍል ሀ ለሚሳተፉ ልጆች ወላጆች በኦክቶበር 30/2017 ወይም ከዛ በፊት ያከፋፍላል፡፡